# ለጥገኞች ከተሰጠው ቤት ስለመልቀቅ

## በሌስተር የስደተኝነት ፍቃድ ለተሰጣቸው መመሪያ

### መግቢያ

ይህ ሰነድ በቅርብ ጊዜ የስደተኝነት ፍቃድ ለተሰጣቸው ሰዎች በሚቀጥለው ሂደት የኑራቸውን ሁኔታዎች ለመርዳትና ለመምከር ያለመ ነው። ፍቃዱን ካገኙ በ28 ቀናቶች ውስጥ ሆም ኦፊስ የሰጥዎትን ማረፊያ ቤት ለቀው እንዲወጡ ይገደዳሉ። ይሄ ብዙ ጊዜ እንደማይሰጥዎት እንረዳለን ስለዚህም የተሰጥዎትን ማረፊያ ከለቀቁ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብዎት በፍጥነት ማቀድ መጀመር በጣም ያስፈልጋል።

ቀጣይ እርምጃዎ ሊሆን የሚገባው:

1. የባንክ አካውንት ይክፈቱ: ዮኒቨርሳል ክሬዲት ለመቀበል፣ ለስራ ክፍያ ለማግኘት እና/ወይም የቤት ኪራይ ለመክፈል ይህንን ማድረግ ያስፈልግዎታል።
2. ዮኒቨርሳል ክሬዲት ይጠይቁ: ይሄ መንግስት ገቢ ለሌላቸው ወይም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች በየወሩ የሚከፍለው ክፍያ ነው። ይሄንን እንዴት መጠየቅ እንደሚችሉ ክጆፕ ሴንተር በመሄድ እገዛ ማግኘት ይችላሉ።
3. ስራ ይፈልጉ: ጆፕ ሴንተር እና በሌስተር የቅጥር ማዕከል ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ
4. ቤት ይፈልጉ: ይህም ምናልባት ፍላት ውስጥ ያለ አንድ ክፍል ወይም ከሌሎች ጋር በጋራ የሚኖሩበት ቤት ሊሆን ይችላል

ሌስተር ውስጥ ቤት ለማኘየት በጣም ከባድ ነው። የቤት ኪራይ ዋጋ ከፍተኛ ነው፣ ተመጣጣኝ ዋጋ የሚከፈልባቸው የካውንስል ቤቶች ወረፋ ለማግኘት በጣም ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል።

ካውንስሉ ምናልባትም መጠለያ ላያገኝልዎት ይችላል እና የራስዎን የሆነ መጠለያ መፈለግ በጣም አስፈላጊ ነው። ለአጭር ጊዜ ከጓደኛ ወይም ከዘመድ ጋር መቆየትን ማሰብ ይኖርብዎታል። ነገሮች ከተመቻቹልዎት በኋላ እና የተሻለ ገንዘብ ሲያገኙ እና በቋሚነት ለረጅም ጊዜ የሚኖሩበት ቦታ ካገኙ በማንኛውም ጊዜ ተመልሰው መውጣት እንደሚችሉ ያስታውሱ።

**አስፈላጊ**

የእርስዎን ቢ አር ፒ (በጣት አሻራና በፎቶግራፍ የተደገፈ የመኖሪያ ፈቃድ) ካርድ ካልተቀበሉ ወይም በቢ ፒ አር ካርድዎ ላይ የተመዘገበው ስህተት ካገኙበት በተቻለዎት ፍጥነት የማይግራንት ሄልፐ ላይንን ያነጋግሩ፣ እነሱ ይህ ነገር እስኪስተካከል ድረስ አሁን ባሉበት መጠለያ እንዲቆዩ ፍቃድ መጠየቅ ስለሚችሉ።

ከላይ ያለውን መንገድ ከተከተሉ የተስተካከለ መረጃ የያዘውን ቢ አር ፒ እስኪያገኙ ድረስ አሁን ካሉበት መጠለያ እንዲለቁ መደረግ የለቦትም።

## የባንክ አካውንት ያውጡ

የኤን ኤ ኤስ ኤስ (ናስ) መጠለያዎትን ከመልቀቅዎ በፊት በተቻለዎት ፍጥነት የባንክ አካውንት ያውጡ። ዮንቨርሳል ክሬዲት እና/ወይም ስራ ሲጀምሩ ደመዎዝ/ወይም ክፍያ የሚቀበሉት በዚህ በባንክ አካውንት ነው የሚሆነው።

የተለያዩ ብዙ ባንኮች አሉ። የዲጂታል ባንክ አገልግሎት ያለው አካውንት ለማውጣት ከሁሉም ቀላሉ ነው።

የስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻዎ በተጨማሪም ስለራስዎ ማንነት እና ስለአድራሻዎ ማረጋገጫ የሚሆን ሰነድ ማቅረብ ይኖርብዎታል።

የማንነት ማረጋገጫ ሰነድ የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላል:

- ፓስፖርት
- ባዮ ሜትሪክ የመኖሪያ ፈቃድ
- የኢሚግሬሽን ፍቃድ የተሰጠበት ሰነድ

የአድራሻ ማረጋገጫ ሰነድ የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላል:

- ከሆም ኦፊስ ድብዳቤ
- የቅርብ ጊዜ የከፈሉበት ቢል (የሙብራት፤ የጋስ ወይም የመሳሰሉት)

የስደተኞች ካውንስል (ሪፊዮጂ ካውንስል) በእንግሊዘኛ እና በሌሎች ቋንቋዎች ዝርዝር የመመሪያ ሰነድ አዘጋጅቷል:

https://www.refugeecouncil.org.uk/latest/news/refugee-council-launches-new-guide-to-help-refugees-open-a-bank-account/

እስካሁን ድረስ የባንክ አካውንት ከሌለዎት እና በአሁኑ ጊዜ አድራሻ ባይኖርዎትም የባንክ አካውንት መክፈት የሚችሉባቸው የተወሰኑ ባንኮች አሉ። ኢንተርኔት ላይ ስለነዚህ አማራጮች መፈለግ ይችላሉ ወይም የስደተኞች እገዛን ምክር ከማይግራንት ሄልፕ መጠየቅ ይችላሉ።

# ዮኒቨርሳል ክሬዲት ይጠይቁ

ዮኒቨርሳል ክሬዲት መንግስት አሁን ስራ ለሌላቸው፣ መስራት ለማይችሉ ወይም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች በየወሩ የሚከፍለው ክፍያ ነው። የቤት ኪራይ እና ስራ እስኪያገኙ ድረስ ያሉብዎትን ወጪዎች የሚሸፍኑበት መንገድ ስለሆነ በተቻለዎት ፍጥነት መጠየቅዎ አስፈላጊ ነው።

**እንዴት መጠየቅ ይችላሉ**

በኦንላይን አካውንት መፍጠር አለብዎት: https://www.universal-credit.service.gov.uk/start

ዮኒቨርሳል ክሬዲት ከማግኘትዎ በፊት የባንክ አካውንት ማውጣት አለብዎት።

**ለመመዝገብ ምን ያስፈልግዎታል**

- የባንክ አካውንትዎ ዝርዝር መረጃ
- የኢሜል አድራሻ
- የሚገኙበት የስልክ ቁጥር

**ማንነትዎን ማረጋገጥ አለብዎት። ከነዚህ ውስጥ (ሁሉንም ማሟላት ላያስፈልግዎ ይችላል)**

- በጣት አሻራና በፎቶግራፍ የተደገፈ የመኖሪያ ፈቃድ (ቢ አር ፒ)
- የመንጃ ፈቃድ
- ፓስፖርት
- የክፍያ ወይም የብድር ካርድ
- የደሞዝ ክፍያ ማስረጃ ወይም P60

**ከነዚህ ውስጥ በየትኛው ላይ መረጃ ማቅረብ ያስፈልግዎታል (እርስዎን የሚመለከት ከሆነ)**

- ስለ ቤትዎ (ምን ያህል ኪራይ እንደሚከፍሉ)
- ምን ያህል ገቢ እንዳለዎት (የክፍያ ማስረጃ)
- የመስራት ሁኔታዎን የሚጎዳ የሰውነት ወይም የጤና ጉደለት
- ማንኛውም ያስቀመጡት ገንዘብ ካለ

**በመጥይቅዎ ላይ እርዳታ**

በሚጠይቁበት ጊዜ እርዳታን ከፈለጉ ወይም በኦንላይን መጠየቅ ካልቻሉ ዮኒቨርሳል ክሬዲት ስልክ መስመር: 0800 328 5644(በዚህ ስልክ ቁጥር ለመደወል ነፃ ነው) በስልክ መጠየቅ ይችላሉ።

## ስራ ይፈልጉ

በዩኒቨርሳል ክሬዲት ሁሉንም ወጪዎችዎን መሸፈን ከባድ ነው ስለዚህም እራስዎን መደገፍ የሚችሉበትን ስራ መፈለግ በጣም አስፈላጊ ነው።

**የስራ ማዕከል**

የስራ ማዕከል ለስራ እንዲዘጋጁ፣ በመፈለግ እና ስራ በማፈላለግና ካገኙም በኋላ ምን ያህል በስራው እንደገፉበት የሚያግዝዎት ይሆናል:

https://find-your-nearest-jobcentre.dwp.gov.uk/search.php

**ሌስተር የቅጥር ማዕከል**

ሌስተር የቅጥር ማዕከል የስራ ማስታወቂያዎችን ያወጣል

https://www.leicesteremploymenthub.co.uk/ (ስራ ፈላጊን ይንኩ)

**ትዊን የስራ ቅጥር እና ስልጠና**

2ኛ ወለል, 60 Charles St, Leicester LE1 1FB

በዩ ኬ ላሉ ስራ ፈላጊዎች፣ ቀጣሪዎች እና ወጣቶች ስልጠና እና አገልግሎት መስጠት

ስልክ ቁጥር: 020 8269 5695

**ሴንት ሙንጎስ የቅጥር አገልግሎት**

የቅጥር አገልግሎት ለስራ ፈላጊዎች 1-2-1 ጊዜዎችን ያመቻቻል። ቡድኑ በስራ ፍለጋ እና ማመልከት ላይ ድጋፍ ያደርጋል።የቃለመጠይቅ ልምምድ፣ የስራ ምደባን እና ቀጣሪ ሊሆኑ የሚችሉትን መጎብኘትን በማቅረብ "ለስራ ዝግጁ" በማድረግ ይረዱዎታል። ቅዱስ ሙንጎ በተጨማሪም የመጀመሪያዎቹን ሳምንታቶችን ወደስራ የሚደረግ ጉዞ እና የስራ ልብስ ካስፈለግዎ የተወሰነ የገንዘብ እርዳታ። ቡድኑ በተጨማሪም የተቀበሉት ስራ ላይ መስራት ያለውን ጥቅም እና ተፅዕኖ ላይ ግልፅ የሆነ ምክር ለመስጠት የሰለጠኑ ናቸው።

በቅዱስ ሙንጎ አገልግሎት ፈላጊዎች በዩ ኬ ውስጥ የመስራት መብት አላቸው እና ለማጣቀሻ የሰራተኛቸውን/ድጋፍ ሰጪያቸውን ዝርዝር መረጃ ያቀርባሉ።

ለተጨማሪ ጥያቄ ወይም ድጋፍ ለመጠየቅ ኤሜል recoverycollegeleicester@mungos.org

## ቤት ይፈልጉ

በዩ ኬ የቤት ችግር አለ። የኪራይ ዋጋ በታሪክ ከፍ ያለበት ነው እና ተመጥጣኝ የኪራይ ክፍያ የሚከፈልባቸው የቤቶች እጥረት አለ። የሌስተር ከተማ ካውንስል በአካባቢው የቤት ችግር እንዳለ ይፋ አድርጓል።

ቤት የሌለዎት እና በፍጥነት ቤት የሚፈልጉ ከሆነ የካውንስሉን ወይም የሃውሲንግ አሶሴሽን *የቤቶች ማህበር ቤትን) የማግኘት እድልዎ ዝቅተኛ ነው።

ሌስተር ውስጥ በአጭር ጊዜ የካውንስሉን ቤት ማግኘት በጣም ከባድ ነው እንደውም የማይቻል አይነት ነው። በሌስተር የማህበረሰብ ቤት ለማግኘት የጥበቃ ጊዜ እና የቤት መጠየቂያ ከተመዘገቡ በኋላ ምን እንደሚፈጠር በተደጋጋሚ ለተጠየቁ ጥያቄዎች ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት: https://www.leicester.gov.uk/your-community/housing/apply-for-housing/guidance-and-faqs/faqs-about-what-happens-after-your-housing-application-is-registered/

ይህም ማለት በሌላ መንገድ መኖሪያ ቤት መፈለግ ይኖርብዎታል ማለት ነው።

በአብዛኛው የግሉ ዘርፍ አከራዮች (የመኖሪያ ቤት አከራዮች, ግለሰብ የቤት ባለቤት) ነው የሚሆነው ነገር ግን እስከተስማማዎ ደረስ ከቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ወይም የመጠለያ ድጋፍ አድራጊ ሊሆንም ይችላል። እባክዎትን ይህንን ነተመለከተ የሚከተለውን ክፍል ለተጨማሪ ማስረጃ ያንበቡ

### በግል የኪራይ መኖሪያ

ከቤት አልባነት ለመገላገል ጥሩው እና ፈጣኑ አማራጭ የግሉ ዘርፍ አከራይ ነው።

በግል ኪራይ መኖሪያ ማለት የቤት ባለቤት ከሆኑ የቤት አከራይ መከራየት ነው። በጊዜ ገደብ ያከራይዎታል እና የቤት ኪራዩን ክፍያ በቀጥታ ለአከራይዎ ይከፍላሉ። ይሄኛው በአብዛኛ ለእርስዎ የሚሆንዎት ፈጣኑ እና ቤት የሚያገኙበት መንገድ ሊሆን ይችላል። በግል መከራየት ካለው ጥቅም ውስጥ በቶሎ ቤቶችን ማግኘት መቻል እና የሚኖሩበትን ቦታ ለመምረጥ ብዙ አማራጭ መኖሩን ያጠቃልላል።

የአካባቢው ቤቶች ተቆራጭ ክፍያ(የቤት ክፍያ ጥቅም) ከሚከፈለው አማካኝ ክፍያ አንፃር ዝቅተኛ ነው ስለዚህም ቤት ለማግኘት በጣም ብዙ ፍለጋ ማድረግ ያስፈልግዎታል ቢሆንም ግን ቤቶችን በአቅምዎ እንዲሆኑ ለማድረግ በአብዛኛው ግዜ ድጋፍ ማድረግ እንችላለን።

### የግል ኪራይ ቤቶችን የት ማግኘት ይችላሉ

- በከተማው ቢቶች የሚይስከራዮ ኤጀንሲዎች
- የአካባቢው ጋዜጣ ለምሳሌ ሌስተር ሜርኩሪ እና የማህበረሰብ ማዕከል፣ ቤተ-መፃህፍት ወይም ሱቆች
- ኦንላይን የቤት ኪራይ ማሳታወቂያዎች – Zoopla፣ Rightmove እና Spareroom ታዋቂ ናቸው

በተመሳሳይ ሰዓት የተለያዩ ቤቶችን ማየት ጠቃሚ ነው ምክንያቱም ቤቶች ቶሎ ነው የሚከራዩት እና ማስታወቂያ ከወጣባቸው ቤቶች አንዳንዶቹ ላይገኙ ይችላሉ።

የፍለጋ ሂደቱን ለማቅለል ከጓደኛ ወይም ከሚያውቋቸው ሰዎች ጋር መፈለግ ጥሩ ነው።

የግል ኪራይ ዋጋው ውድ እንደሆነ እናውቃለን ነገር ግን በአቅምዎ የሚሆኑ ቤቶችን አግኝተው በደስታ እንዲኖሩ የሚያግዙ ብዙ አይነት መንገዶች አሉን። ሁልጊዜም ቤትዎ ተመጣጣኝ ዋጋ፣ ለዕርስዎ በቂ ስፋት ያለው እና በጥሩ ሁኔታ ያለ መሆኑን እናረጋግጣለን።

**መሰናክል የሆኑ ነገሮችን በማስወገድ እንረዳለን:**

- በአቅምዎ ያልሆነ መኖሪያ
- ከፍ ያለ ገንዘብ ለዲፖዚት
- የቤት አከራይ ላንድ ሎርዶች የሚያገኙትን ድጎማ እንደ የቤትኪራይ መቀበል

**እነዚህን መሰናከሎች እንዴት እናስወግዳለን:**

- በተለያዩ መንገዶች ለአከራዮች ጥቅማጥቅም በማመቻቸት
- ቅድመ የኪራይ ክፍያ ወይም ዲፖሲት በማቅረብ.
- ከሚፈወድሎት የቤት ክፍያን እነርሱ የጠቀሱትን የኪራይ መጥን በማቀራረብ
- ነገሮች እንዲስተካከሉ የኪራይ ድጋፍ ለዕርስዎ እና ለአከራይዎ በማድረግ

**በጀት**

ላጤ እና እድሜዎ ከ35 ዓመት በታች ሆኖ ልጅ ከሌለዎት ከዮነቨርሳል ክሬዲት የሚያገኙት የቤት ገንዘብ ድጋፍ 'ከሼርድ (በጋራ) የሚኖርበት ቤት ከሚከፈለው ጋር' የተመጣጠነ ነው የሚሆነው፡

ይህም ማለት የመከፈልሎት ገንዘብ ባጀት  በጋራ መኖሪያ ቤት/ህንፃ ላይ ላለ ለአንድ ክፍል የመሆን እድሉ ከፍተኛ ነው።

የሚያገኙት የከፍያ መጠን የአካባቢው ባለስልጣን የቤት ደጉማን በተመለከት በሚያወጣው መሰረት ይሆናል። ይህ እንዴት በተለያዩ ቦታዎች እንደሚለያዩ ለማወቅ https://www.leicester.gov.uk/ ይጎብኙ እና 'ሎካል ሆውሲንግ አላዋንስ' (Local Housing Allowance)ብለው ይፈልጉ።

**ምን ማድረግ ይጠበቅብኛል?**

ቤት አልባ ከሆኑ ወይም ቤት አልባ የመሆን ስጋት ውስጥ ካሉ እነዚህን ሶስት ሂደቶች ይከተሉ:

- የቤቶች አማራጮች አገልግሎትን በ 0116 4541008 በማግኘት የቤት አልባ ግለሰብ ማመልከቻ ይሙሉ እና ስለቤት አማራጮች ምክር ያግኙ።

- በሌስተር ውስጥ እኛ ልንረዳዎት በምንችለው የቤት ክፍያ መጠን ውስጥ ያሉ ቤቶችን ይፈልጉ:

  - የጋራ ወይም አንድ ክፍል (ከ35 ዓመት በታች) - ከፍተኛው የኪራይ ዋጋ £455
  - 1 ክፍል ቤት - ከፍተኛው የኪራይ ዋጋ £605
  - 2 ክፍል ቤት - ከፍተኛው የኪራይ ዋጋ £760
  - 3 ክፍል ቤት - ከፍተኛው የኪራይ ዋጋ £910
  - 4 ክፍል ቤት - ከፍተኛው የኪራይ ዋጋ £1,200

•ቤቱን ካዩት በኋላ እና አከራይዎ/አገናኙ ነገሮችን ለመጨረስ ከተስማሙ በኋላ የቤቶች አማራጭ አገልግሎትን በ 0116 4541008 ወይም የግሎትን የኬዝ ዎርከር ሰራተኛን ያግኙ። ከዛ በኋላ እኛ እንደርስዎ ሆነን የላንድ ሎርድ አከራይዎን እናናግራለን እና ስለምናቀርባቸው የዋጋ አማራጮች እናወራቸዋለን።

## የጎዳና ተዳዳሪ እርዳታ

ጎዳና ተዳዳሪ የሆነ ሰው የሚያውቁ ከሆነ በ 0300 500 0914 ይደውሉ ወይም በድህረገፅ ይጠቁሙን፡ www.thestreetlink.org.uk

ቤት አልባ ሊሆን ያለ ግለሰብን የሚያውቁ ከሆነ የሌስተር ቤት አልበኝነት መከላከል አገልግሎትን በ 0116 454 1008 ደውለው ማነጋገር ይችላሉ።

የጎዳና ተዳዳሪ ከሆኑ ምክርና ድጋፍ በ 0116 2212770 በመደወል ማግኘት ይችላሉ። ይህ ቁጥር በቀን 24 ሰዓት በሳምንት 7 ቀናት ክፍት ነው።

## ሙቀት ቦታዎች እና የቀን ማዕከሎች

ምክር፣ ምግብ እና መታጠቢያ በማቅረብ ድጋፍ የሚያደርጉ ቦታዎች አሉ:

The Bridge (ዘ ብሪጅ) – ከቤት አልበኝነት ወደ ተስፋ, የተስፋ ማዕከል 43 Melton Street, Leicester.

ሰኞ, ማክሰኞ, ሀሙስ እና አርብ 9.30am-2.30pm። ቅዳሜ 9am-1pm

The Y Advice and Support Centre (YASC)(ዘ ዋይ አድቫይስ ኤንድ ሰፖርት ሴንተር), 165 Granby Street, Leicester.

ከሰኞ እስከ አርብ 8-10am

Help the Homeless(ሀልፐ ዘ ሆምለስ), 9 Abbey Street, Leicester.

ሀሙስ 12ቀን-4pm

The Centre Project(ዘ ሴንተር ፕሮጀክት), 1 Alfred Place, Leicester.

ማክሰኞ, ሀሙስ እና አርብ 10am-4pm

የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡትን ዝርዝር www.leicesterhomelesscharter.co.uk/news/meals-for-people-experiencing-homelessness ማግኘት ይችላሉ

## ሌሎች እርዳታ ሰጪ ተቋማት

የሌስተር ሲቲ መጠለያ(Leicester City of Sanctuary), 43 Melton Street, Leicester.

ኢሜል: contactus@leicester.cityofsanctuary.org

የብሪትሽ ቀይ መስቀል ስደተኞች አገልግሎት(British Red Cross Refugee Service), 27 East Street Leicester.

ኢሜል: RefugeeSupportWY@redcross.org.uk

የዘር እኩልነት ማዕከል(The Race Equality Centre), አንደኛ ወለል, Highfields Centre, 96 Melbourne Road, Leicester, LE2 0DS

ስልክ: 0116 204 2797

የዘር እኩልነት ማዕከል በቤት አገልግሎት፣ በጥቅማጥቅም እና በጠቅላላ ደህንነት ዙሪያ ድጋፍ ይሰጣል። በየሳምንቱ በመገናኘት የመዝናናት እና የንግግር ቡድን አላቸው እና በመሰባሰብ እና 'ቃራቡኒ(Karabunui)' ካፌ ብዙ የበጎአድራጎት ስራን ይሰራሉ። ማዕከሉ በተጨማሪም ለጉዞ ቪዛ፣ ለፓስፖርት ማጠናቀቅ፣ ወዘተ የስደተኞች አገልግሎትን በቅናሽ ዋጋ ይሰጣሉ።